# የብሽቆች ፖለቲካ አመክኖው ብሽሽቅ ነው

ሄኖክ የሺጥላ

ሻዕቢያን በተመለከተ ያለኝን አቋም ስገልጥ ዛሬ ኣዲስ ነገር ኣይደለም ። ሻዕቢያን በቅጡ እና ቀላል ባለ መልኩ ለመረዳት ተስፋዬ ገ/ኣብን መረዳት ለኔ በጣም ግልፅ እና አጭሩ መንገድ ይመስለኛል ። ውስጡን **(** ጉዱን እና ጉዳንጉዱን **)** ለማወቅ የሚሻ ሰው ግን በኤሪትሪያ ቴሌቪዥንን እና መሰል የሻዕቢያ ሚዲያዎች እለት እለት የሚቀርቡትን ፕሮግራሞች ማየት በቂ ነው። በእርግጥ ለመረዳት አቅም እንደሚጠይቅ ኣውቃለሁ።

**«**በሁለት ነጥቦች መሃከል ያለው ኣጭሩ መንገድ ቀጥታ መስመር ነው**»** የሚለውን የ ኒውቶኒያን ፊዝክስ መለመሉን ያስቀረው ኣልበርት ኤንስታይን በምድር ላይ ፈጣኑ ነገር **(** ማለትም ብርሃን **)** የሚጓዝበት ወይም የሚከተለው የጉዞ ጎዳና ቀጥታ መስመር እንዳልሆነ በማስረዳት ፥ ፈጥኖ የደረሰው ቀጥ ብሎ ባለመሄዱ ነው ይለናል ። ወይም ብርሃን በኣግድሞሽ የተቀነፈ ምህዋር **( curve linear path )** ን ይከተላል ይለናል ። ይህንን ሃሳብ ፈረንሳዊው የሂሳብ ሊቅ ሊበነዝ ከአንስታይን ቀደም ብሎ ሊያስረዳ እንደሞከረ ጠቋሚ መዛግብቶች ኣሉ ። ምን ለማለት ነው ፥ ቀጥ ብሎ መሄድ የለመደና በቀጥታ መስመር ቶሎ የደረሰ ፥ ከሁሉም ነገር የፈጠነ ነው ማለት ኣይደለም ። ኣሁን ያለን ብቸኛ የትግል ኣማራጭ ሻዕቢያ ነው ማለት ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ **(** በኔ ስሜት ለአማራ **)** ጥሩ ይመኛል ማለት ኣይደለም ። ወይም ደሞ በኤርትራ በኩል ብቻ የሚደረግ ትግል ነው ወያኔን የሚጥለው ማለትም ኣይደለም ።

ወያኔ በኤርትራ እርዳታ ኣዲስ ኣበባ ስለገባ ሁሉም በዚያ በኩል ሊገባ ይችላል ብሎ ማሰብ ፥ በቀጥታ መስመር ተጉዞ ፈጥኖ የደረሰው ኣሎሎ ፥ ብርሃንንም እንዲያ ካልተጓዝ ኣትፈጥንም ብሎ የመሞገት ኣይነት ስሜት ነው ለኔ የሚታየኝ። እንደሚመስለኝ ነፃነት የጠማው ህዝብ ትልቁ ችግር ያለው እዚህ ላይ ነው ። ጥማቱን ለማርካት ሲል በውሃ አቅላሚ **(** ኣልጌ**)** የዳበረም ውሃ ቢሆን ብንጠጣ ምን ችግር ኣለው ብሎ ይሞግትሃል ። በዚያ ላይ ሻዕቢያን መንካት ግንቦት ሰባትን መንካት ኣድርገው የሚያዩም ብዙ ናቸው ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል **?** የሻዕቢያ እና የግንቦት ሰባት ግንኙነት እኔ እስከማውቀው ድረስ የጌታ እና የሎሌ ኣይመስለኝም ። ሻቢያ ሲነካ ብርድ ብርድ ሊለን የሚገባው በሁለቱ ኣካሎች መሃከል ያለው ትስስር ያ እንደሆነ ብቻ ነው ። በቀደመው ጥሁፌ ላይ ኣስቀምጫዋለሁ ። ሻዕቢያ የራሱን ጥቅም ከማስጠበቅ ኣንፃር ኢትዮጵያዊያን የወያኔ ተቃዋሚዎችን ድጋፍ ይሰጣል ።

የሻዕቢያ ጥቅም ምንድን ነው የሚለውን ስንመለከት ግን ፥ በሱ ግንዛቤ ጥቅሜን ኣያስከብሩም ብሎ የሚያስባቸውን ኣካሎች፥ የራሱን የሻዕቢያን ቋንቋ ብጠቀም **«** የሙቶ ኣመት የቤት ስራ **»** ሰጥቶ እርስ በእርሳቸው እያናቆረ ፥ ጠቡ ከውስጥ የመጣ በማስመሰል ኣንድ ጋት ወደፊት እንዳይራመዱ ኣድርጓል ፥ ወደፊትም ያደርጋል ። ለምሳሌ ስለ ሻዕቢያ ከምትቆረቆሩት ውስጥ ስንቶቻችሁ **«** ኣሰብ የኢትዮጵያ ኣይደለም **»** ብላችሁ ታምናላችሁ **?** ሁላችሁም ኣታምኑም ። ሻዕቢያ ደሞ ይሄንን የሚያምን ተቃዋሚ እስከሚመጣ ድረስ ትግሉን ይጠነስሳል ፥ ትግሉን መልሶ ያፈርሳል ። እንዲህ ኣይነት ተቃዋሚ ይመጣል ወይ ። ኣዎ**!** መቼ **?** የ ኢትዮጵያ ህዝቦች እርስ በእርሳቸው ተባልታው እና ተነካክሰው ፥ በጋራ ለመኖር የሚያስችል ኣንዳችም እንጥፍጣፊ ፍላጎት ሲነጥፉ ፥ ስለ ኣሰብ ምን ኣገባኝ የሚል ተቃዋሚ ይወለዳል ። ምናልባትም ተወልዷል ።

ከነዚህ የጋራ እና የኣብሮ መኖር ምሳሌነት ውስጥ እንደ ኣንድ እሴት ተደርጎ የሚወሰደው የአማራ ህዝብ በኣንድነት ላይ ያለው ኣቋም ነው ። ይህ ለሻዕቢያም ሆነ ለወያኔ አደገኛ ነገር ስለሆነ ይህንን መንፈስ ለማጥፋት የመንፈሱን ባለቤት ማጥፋት የሚለው ኣብይ ሃሳባቸው ነው። ገ/መድህን ኣርዓያ የሚነግርህ ያንን ነው ፥ የበርሃ ውሏቸው እና የትግል ታሪካቸው የሚነግርህ ያንን ነው ።

ምፅዋ ላይ የተማረኩ የደርግ ወታደሮችን በጥይት ረሽኖ የከመረው እኮ ወያኔ ኣይደለም **!** ነው እንዴ **?** በ ሂውማን ትራፊኪንግ **(** በየመን ፥ በግብፅ ሲና በርሃ ፥ በሊቢያ እና መሰል ቦታዎች ላይ ከወያኔ እኩል ኢትዮጵያዊያኖችን የሚሸጡት የሻዕቢያ ሰዎች መሆናቸውን ማን ነው የማያውቅ **)**። ኣማራጭ ማጣት እውነትን እንድንክድ ኣያደርገንም ። እንክርዳድን ፍሬ

ኣያደርገውም ። በሻዕቢያ በኩል የሚካሄደው ትግል ይሳካ ዘንድ ፥ በቅድመ ወያኔ- ወ ሻዕቢያ የጫጉላ ሽርሽር ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ላይ የነበረው ንብረትን የመቆጣጠር ኣቅም ብቻ ሳይሆን ፥ በሂደቱ ከንግድ ፉክክሩ እንዲወጡ ፥ ከስራ እንዲባረሩ ፥ እንዲታሰሩ የተደረጉ የአማራ ብሄር ተወላጆች በወያኔ ሳይሆን በሻዕቢያ ጋሻ ጃግሬነት የተፈፀመ መሆኑን መካድ ይጠበቅብናል ማለት ነው ? ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ኣንድነት የሚያምን ከሆነ የኢትዮጵያን ኣንድነት ለመናድ እንደ ኦነግ ያሉ ድርጅቶችን የትግል ፍቃድ እንደምን ሰጠ።

ሀሳባችን አንድ እና አንድ ነው ። ወያኔና ሻዕቢያ በአመለካከትም ሆነ በስራት ይህ ነው የሚባል ሰዋዊ ልዩነት የላቸውም ። ልዩነቱ ሻቢያ በወያኔ የፖለቲካ ቁማር መበላቱ ብቻ ነው ። ይህንንም በቀል ( ዲካርት ስቴት ) ለመቀየር ሲሉ ፥ ( ብሎም ረጅም ጦር ባይወጉበትም ማስፈራሪያ ነው ) ስለሚባለውም ሲሉ ፥ እዚህም እዚያም ተቃዋሚዎችን ሲረዱ ይታዩ ይሆናል ። ይህ ማለት ተቃዋሚዎቹ ቁማርተኛ ናቸው ማለት ኣይደለም ። ብዙ የማከብራቸው ትልልቅ ሰዎች ዛሬም በርሃ ውስጥ ኢትዮጵያን ብለው መከራቸውን እያዩ እንደሆነ ስለማውቅ !

ትልቁ ችግር ያለው የብሽቆች ፖለቲካ አመክኖው ምክንያታዊ ሃሳብ ማቅረብ ሳይሆን በ ብሽሽቅ መጠመድ ስለሆነ እንጂ !